# <u>መልዕክተ ኦባንግ</u>

**“የምንታገለው ለመንደር ወይስ ለሐገር? መታገል ያለብን ለሐገር አንድነት ነው፣ ሐገር ከሌለች መንደር አይኖርምና።”**

**አቶ ኦባንግ ሜቶ ‘የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄ’ መስራች ከተናገሩት ተተርጉሞ የተወሰደ**

አተኩሮ ላየው ቅንነቱን ለመረዳት ጊዜም አይፈጅም፡ በተኮላተፈና ጥርት ባለ አማርኛውም ሆነ አቀላጥፎ በሚናገረው እንግሊዝኛው በጨዋ ኢትዮጵያዊነት ከአፉ የሚወጡት ቃላት ልብ ውስጥ ጠልቀው ይገባሉ። ዘወትር በሄደበት ሁሉ የሚናገረው ኢትዮጵያዊነትን ነው፡ ሊነግረን የሚፈልገው ልዩነታችንን ወደጎን በመተው እርስ በርሳችን በመነጋገር ችግሮቻችንን እየፈታን አንድነታችንን ማጠንከር እንዳለብን ነው። በዘርና በመሳሰሉት ዛሬ ገዥው ፓርቲ የሚያራምዳቸውን የጎሳ ፖለቲካ ውስጥ ገብተን በመዳከር እርስ በርሳችን እንዳንጠላላና እንዳንቀያየም ይማጸነናል። የነገዪቱ ኢትዮጵያ እጣ ያሰጋኛል፤ ዛሬ ካልተባበርን፣ ኢትዮጵያዊ ነን የምንል ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘን መሔድ ካልቻልን፣ ነጻና ፍትሕ የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን ለማየት የምንጓጓበትን ጊዜ ያርቅብናል እንጂ አያቀርብልንም ይለናል ኦባንግ፡

ኦባንግ ሜቶን ዛሬ ከሰሜን አሜሪካ እስከ አውሮፓ፣ ከአፍሪካ እስከ አውስትራሊያ የማያውቀው ኢትዮጵያዊ አለ ለማለት ያስቸግረኛል። የሰላም ጥሪው፣ የፍቅር ጥሪው ከጫፍ እስከ ጫፍ አስተጋብቷል፡ የነገዪቱን ኢትዮጵያ ሁላችንም አንድ ሆነን ነው የምናቆማት፡ አድሎ የሌለባት የአንድ ዘር የበላይነት የማይታይባት፡ ሁሉም ሰብአዊነቱ ተከብሮና እኩል ዜጋ ሆነን የምንኖርባትን ሀገር ለማቆየት ከፈለግን በአንዲት ኢትዮጵያ ጥላ ስር መሰባሰባችን ግድ ይላል።

ኦባንግ እንዲህ ይላል፣ ስንወለድ ከዚህ ጎሳ እንሁን ብለን ፈልገን አልተወለድንም፡ ወይንም ትግሬ ወይም አማራ ወይም ኦሮሞ ወይም ወላይታ ወይም አኙዋክ ለመሆን ምርጫ አልቀረበልንም፡ ስንወለድም ይህንን ቋንቋ እንናገር ብለን ፈልገን አላደረግንም፣ ወደዚህ ዓለም ስንመጣ እነዚህን ሁሉ ይዘን አልመጣንም። አባባሉ ትክክል ነው፡ ከየትኛውም ጎሳ ልንወለድ ወይንም የተወለድንበትን ወይም ያደግንበትን ቋንቋ መናገራችን ኢትዮጵያዊነታችንን በምንም ዓይነት ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባ አይችልም።

ኦባንግ በተለያዩ የሰሜን አሜሪካ፣ አሜሪካ እንዲሁም በአውሮፓ አገሮች በመዘዋወር የተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ይህንኑ የኢትዮጵያዊነት፣ የአንድነትን፣ የመተባበርን እና የመከባበር መልእክቱን በተገኘባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ከመናገር ወደ ኋላ ያለበት ጊዜ የለም። በነዚህ በተገኘባቸው ስብሰባዎቸ ላይም የታዘባቸውን ለትምህርት እንዲሆነን በምሳሌነት ይጠቅስልናል። ከታዘባቸውም ውስጥ በተለይ በጣም ያሳዘነውና ያስገረመው በተለያዩ ጊዜያት ተጋብዞ ንግግር ለማድረግ በኦጋዴንና በኦሮሞ ተወላጆች ባዘጋጁት ስብሰባ ላይ በተጋበዘበት ወቅት የስብሰባው ተካፋዮች በሙሉ በእጃቸው ባንዲራ ያውለበልቡ እነደነበርና ባንዲራዎቹ በሙሉ የክልሉ እንደሆኑ ነገር ግን አረንጓዴ፤ ቢጫ፤ ቀዩን የኢትዮጵያዊነታችን መለያ የሆነው ባንዲራችንን ባለማየቱ ልቡ ክፉኛ እንዳዘነ ነው። ባንዲራ ማንንም አልጨቆነም ፤ ባንዲራ ማንንም አልገደለም ይለናል። እኔም የኦባንግን ሃሳብ እጋራለሁ፡ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላለፉት ብዙ አመታትና አሁንም ድረስ በገዥዎችና በአባሎቻቸው የተለያዩ ግፎች ማለትም የመገደል፣ የመታሰር፣ የመሰደድ እና የመሳሰሉት ሁሉ ሲደርስበት ቆይቷል። ነገር ግን አሁን በምንገኝበት ዓለም በተራቀቀበት ዘመን ያለፉትን እያነሱ መነካከስ እና መባላቱ ምን ጥቅም ሊያመጣ ይችላል? ይልቅስ ተነጋግረንና እርስ በርሳችን መተማመን ፈጥረን ሁላችንም በእኩልነት

የምንኖርባትን አንዷት ኢትዮጵያን ለመፍጠር ብንሯሯጥ ምናልባት የኢትዮጵያን ትንሣኤ የምናይበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ብዬ አስባለሁ።
እዚህ ላይ ለእውነት ስለእውነት ብለን ለሐገራችን እና ለሕዝባችን ጥሩ የተሻለ ጊዜ ለማምጣት የምንታገል፤ ከዚህ በፊትም በትግሉ የተፈተንንም ሆንን ለመፈተን እራሳችንን ያዘጋጀን፤ ለአንድ አፍታ ቁጭ ብለን ያለፉትን ጊዜያት ወደሗላ ዞር ብለን እናስብ፡ ምን ያህል ለእራሳችንም ሆነ ለምንታገልለት ሕዝብ የሚያረኩ ተግባራትን ፈጽመናል? ትግሉንስ ምን ያህል ወደፊት እንዲራመድ አስተዋጽኦ አድርገናል? ይህን አድርጌያለሁ ብሎ የሚያስብ ኢትዮጵያዊ ካለ በጣም ጥሩ ነው። ለእኔ ግን መስራት ከሚገባን 1% እንኳን ሰርተናል ለማለት ይቸግረኛል። በእውነቱ ችግራችን ምነድነው? በእኔ አመለካከት ችግራችን አለመነጋገር፤ አለመወያየት፤ የሌሎችን ሀሳብ መናቅና የእኔ ብቻ ነው ትክክል የማለት፤ የብዙሃኑን ድምፅ አለመቀበል፡ ብሎም አፈንግጠ መውጣትና ሌሎች ብዙ ጥሩ ሥራ ሊሰሩ የሚችሉትን ያልሆነ ስም በመሰጣጠት በመተቸትና ስም በማጥፋት እንካ ሰላንቲያ ውስጥ በመግባት ብዙ ሥራ ሊሰራ የሚችልበትን ጊዜ በከንቱ ማጥፋት ያውም እነዚህ በጣም ጥቂቶቹ ናቸው። እያንዳንዳችን ችግራችን ምን እንደሆነ ጠንቅቀን እናውቃለን ነገር ግን እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከራሳችን በመነሳት ምን ያህል ጥረት ለማድረግ ጀምረናል? እነዴት ባለ መንገድ ሁላችንም እየተነጋገርን እና እየተወያየን በመካከላችን ያሉትን ችግሮች እየፈታን በመተማመን ወደፊት የምንሄድበትን መንገድ መጥረግ እንችላለን?

በዚህ ላይ የራሴን አስተያየት ለመስጠትና መፍትሔ ይሆናል ብዬ የማቀርበው ሃሳብ እንደሚከተለው ነው፣

1. <u>ራስን ማወቅ፦</u> በመጀመሪያ እራሳችንንና አላማችንን በደንብ እንወቅ፡ በምንሰራው ሥራ ላይ በቂ እውቀት አለኝ ከኔ በላይ የሚያውቅ ማንም የለም እኔ ያልኩት ብቻ መሆን አለበት ብሎ መነሳት በራሱ የመጀመሪያው ወደ ጥፋት የሚወስድ በመሆኑ ከዚህ አይነት አስተሳሰብ ራስን ማግለል። በራስ መተማመን በራሱ ምንም ጉዳት የለውም ግን የበለጠ ውጤት የሚኖረው የሌሎቸን ሃሳብ እና ፍላጎት መቀበልና ማስተናገድ የሚችል ተፈጥሮ ሲኖር ብቻ ነው።
2. <u>በውይይት እና በመነጋገር ማመን፦</u> መወያየት መነጋገር እና የሌሎችን ሃሳብ መስማት ከሰሙም በሗላ ይሄ ይጠቅማል ብሎ የሚጠቅመውን መያዝና ወደ ሥራ መተርጎም ወይም ደግሞ የተሰጠው ሃሳብ ለጊዜው ሊጠቅም የማይችል ከሆነ ወደፊት ሊጠቅም ይችላል ብሎ ማሰብና መያዝ አሊያም ሃሳቡን ውድቅ ማድረግ ግን ሃሳቡን ያቀረበውን ግለሰብ አክብሮት መስጠት፡ ግለሰቡም የታዳሚውን ውሳኔ ተቀብሎ አብሮ ለመጓዝ መስማማት።
3. <u>መደማመጥ መቻል፦</u> ብዙውን ጊዜ በተለይ በስብሰባዎች ላይ ችግር የሚገጥመን አንዱ በሚናገርበት ጊዜ ሌሎቻችን ማዳመጥ አለመቻላችን ነው፡፡ ይህንንም ማረጋገጥ የምንችለው ተደጋጋሚ የሆኑ ሃሳቦች ወይንም ጥያቄዎች በተለያዩ ሰዎች ሲሰነዘሩ መታየት፤ አንዳንድ ሰዎችን ከዚህ በፊት በግል ባለን ቅሬታ ወይንም አመለካከት ወይንም ይሄ ደግሞ ምን ያውቃል በሚል ንቀት በተሞላበት ሁኔታ የተነሳ ገና ሃሳባቸውን ሊሰጡ ሲነሱ ከመጀመራቸው በፊት መጨረሳቸውን የምንጓጓ ጥቂት አይደለንም፡ ስለዚህም የሚናገሩት ሃሳብ እንኳን ጥሩ እና ገንቢ ቢሆንም ለማዳመጥ እድል ስላልሰጠነው ጊዜን ከማባከን ውጪ የሚፈይደው ነገር ላይኖር ነው።
4. <u>መተማመን መፍጠር፦</u> አብረን ለመጓዝ እንድንችል መተማመን በመካከላችን መፍጠር ያስፈልጋል፡ ይህም ሊፈጠር የሚችለው በደንብ መተዋወቅ ሲኖር፡ አስተያየታችንን አጥብበን ሳይሆን ሰፋ አድርገን ብዙ ነገሮችን ማየት ስንችል ብሎም እርስ በርሳችን በሃሳብም ሆነ በሌላው መደጋገፍ ስንችል፣ ሰዎችን በቅድሚያ ሰብዕናቸውን (ሰው መሆናቸውን) እንጂ ዘር ጎሳ ቋንቋና ቀለም የመሳሰሉት አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ እነደማያደርግ ተገንዝበን ለአንድ አላማ አብረን እንቁም ያሉንን ወንድሞችና እህቶች በመያዝ ግንኙነታችንን እያሰፋን፣ ካለፈው እየተማርን፣ ዛሬን እየሰራንበትና መጪው

ጊዜ ብሩህ እንደሚሆን በማመን መጓዝ መተማመንን ሊፈጥር ይችላል። ግን ከሁሉም በላይ ቅን ልቦና እንዲኖረን ግድ ይላል።

5. <u>ይሉኝታንና ሐሜትን ማስወገድ፦</u> እኛ ኢትዮጵያውያንን እነደ በሽታ ከሚያጠቁን ነገሮች ውስጥ ይሉኝታና ሐሜት ዋናዎቹ ናቸው፣ ይሉኝታ የሚያስፈልግበት ቦታና ጊዜ ቢኖረውም በተለይ በግል ሕይወታችን አብዝተን ብንጠቀምበትም የማይጎዳን ሲሆን ነገር ግን ከፍተኛ ጥንቃቄን በሚጠይቁና ለሕዝብ እና ለሐገር በሚደረጉ ስራዎች ላይ የሚያመጣው ጉዳቱ እንዲህ ቀላል አይሆንም። አንድን ግለሰብ በጓደኝነትም ሆነ በዝምድና ወይንም በሌሎች ባሉን ቅርበቶች ምክንያት ግለሰቡ በሚሰነዝራቸው አስተያየቶች ወይንም ለሕዝብ እና ለሐገር በሚሰራቸው ሥራዎች ላይ ስህተቶች እያየን በይሉኝታ ተይዘን በጭፍን ድጋፋችንን የምንቸር ከሆነ ልናደርስ የምንችለው ጉዳት ቀላል አይሆንም። ሐሜትም ሌላው ጎጂ የሆነ ፊት ለፊት ከሚመለከተው ጋር ከመነጋገር ይልቅ በጓሮ በር ግለሰቦች በማያውቁት መንገድ የሰሩበትን እንዳልሰሩ፣ የደከሙበትን እንዳልደከሙ አድርጎ ከሌሎች ጋር በመሆን የስም ማጥፋት ዘመቻ ማካሄድ ለሐገርና ለወገን የምናደርገውን ትግል የሚያዳክም እንጂ የሚያጠናክር እነደማይሆን ግልፅ ነው። ለመስራት ቆርጠው የተነሱትንም ሆነ የደጋፊዎቻቸውን ልብ እና ቅስም ሰባሪ ሆኖ ሁሉንም ከትግሉ መንደር የሚያርቅ ዕኩይ ሥራ ሊሆን ይችላል።

6. <u>ድክመትንና ተጠያቂነትን መቀበል መቻል፦</u> በሐገራችን ከድሮም ጀምሮ እንደ ባሕል ይዘነው እስካሁን ድረስ ልናሻሽለው ያልቻልናቸው ሁለት ነገሮች ውስጥ ድክመትን መቀበል እና ለሐገር እና ለወገን ለሚሰሩ ሥራዎች በተለይ በግለሰቦችም ሆነ በቡድን ለሚደርሰው ውድቀት ተጠያቂነትን የመቀበል ልምድ አለመኖር ናቸው። ይህ ደግሞ ባለፉት ጊዜያት ያየናቸው በተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ ለተከሰቱት ችግሮች ተጠያቂ አለመኖሩ በሕዝብና በደጋፊዎች ዘንድ ክፍፍልን ሊፈጥር በቅቷል። ነገር ግን ነገሮችን ከመሸፋፈን እና በውስጥ በአሰራርና በግለሰቦችም መካከል ቢሆን አሉ የሚባሉትን ችግሮች ተወያይተውበት ግልፅ በሆነ መንገድ ያሉትን ድክመቶች ግልፅ አድርጎ ማውጣትና ለችግሩ ተጠያቂ የሚሆኑትን በመረጃ በመደገፍ የማሳወቅ አሰራር ቢኖር ተጠያቂ የሚሆኑትን ቢቻል ተጠያቂነታቸውን አምነው ያለውን ስሕተት አርመው ደጋፊዎቻቸውን ይቅርታ በመጠየቅ የሚሰጡትን አገልግሎት እንዲቀጥሉ የማድረግ አሠራር በመልመድ የቀድሞውን መጥፎ የአሠራር ልምድ መቀየር አስፈላጊ ነው። ቢቻል ለደረሱ ጉዳቶች ተጠያቂ መሆንም ሆነ በሥራ ላይ ድክመት ካለ ድክመትን አምኖ ለተተኪ ቦታውን መልቀቅ ሙሉ በሙሉ በራስ ፍቃደኝነት ቢሆን ይበልጥ ብልህ ያሰኛል በዛውም መጠን ለሐገር እና ለወገን ያለውን ፍቅር የሚያሳይ ይሆናል።

   በተለይ ለብዙ አመታት ቁልፍ ቦታዎችን በመያዝ ምንም ለውጥ ያልታየባቸው አንዳንድ የፖለቲካ መድረኮችን በብዛት እያየን ነው፣ እነዚህ መድረኮች አሠራራቸውን በአፋጣኝ መገምገምና በእውነት ትግላቸው ለዲሞክራሲ ከሆነ ዲሞክራሲያዊ አሰራርን ራሳቸው በውስጣቸው ማስፈንና ድክመት ያለባቸውን ቦታዎችና ግለሰቦች እየገመገሙና ሊሰሩ በሚችሉ እውቀቱና ጉልበቱ ባላቸው እየተተኩ ለውጥ ሊያመጣ ሥራ እንዲሰራ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

እንግዲህ ከላይ የተዘረዘሩትን ለማሟላት አስፈላጊውን ጥረት ካደረግን በኋላ ከማንኛውም አላማችን አንድ ከሆነና የተለያዩ ጥቃቅን ሃሳቦች ቢያለያዩንም ነገር ግን ግባችን አንድ እና ያውም ሐገርን ማዳን ከሆነ በመካከላችን ዋናውና ትልቁን መተማመንን በመፍጠር መንገዳችንን እየጠረግን መሄድ ያስፈልገናል።

## በአሁኑ ወቅትና ሰዓት ለኛ ለኢትዮጵያውያን የሚያስፈልገን ምንድነው?

<u>መወያየትና መነጋገር፡</u>- ኢትዮጵያውያን በአሁኑ ወቀት የውይይት መድረክ በመፍጠር ባሉብን ችግሮች ላይ መወያየት እና ለችግሮቻችን መፍትሔ በመፈለግ አንዱ ሌላውን ጠልፎ ለመጣል ምክንያት እንዳይሆን መፍትሔዎችን መፈለግ ያሻል።
ለምሳሌ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. 'ውይይት ለሰላምና ለጋራ ዓላማ በኢትዮጵያ' በሚል ስም ተጀምሮ በሚቀጥለው ጁን 28 2009 ዓ.ም. ለሶስተኛ ጊዜ በኢትዮጵያውያን መካከል የሚደረገው ውይይት በትልቅ ምሳሌነት ሊወሰድ ይችላል። ሌሎችም ኢትዮጵያውያን ባሉባቸው ከተሞችም ሆነ ክልሎች የዚህን አይነት መድረክ በመፍጠር መነጋገሩ በመካከላችን በደንብ መተዋወቅና ብሎም መተማመን ስለሚፈጥር ይህ ትውውቅና መተማመን ደግሞ ጥሩና ዘለቄታ ያለው ሥራ ለመስራት ትልቅ መንገድ ከፋች ይሆናል።

በእነዚህ ውይይቶች የጋራ ችግሮቻችንን፣ የስብሰባ ባህላችንን (ከሰዓት ማክበር ጀምሮ የሌላውን ሃሳብ እስከማክበር ድረስ)፣ ካለንበትና ከምንኖርበት ሐገር ስላለው ዲሞክራሲ መማርና ማዳበር ስለሚገባን ልምድ፣ ሐገራችንን በልማት ደረጃ እንዴት መርዳት እንደምንችል (ድሃውን ሕዝብ አለንልህ ከአጠገብህ ነን ለማለት)፣ በመወያየትና በመማማር የራሳችንን እውቀት ከማዳበር አልፈን በመካከላችን ሠላም ፈጥረን በሃገራችን ላይ ለውጥ ለማምጣት ጥረታችንን መቀጠል ይኖርብናል። ይህ ውይይት ለግለሰቦች ብቻ ሳይሆን በፓርቲዎች ደረጃም አስፈላጊነቱ ታምኖበት በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት እንታገላለን የሚሉ ፓርቲዎችም ሆኑ ንቅናቄ ቡድኖች ለብቻ የሚመጣ ውጤት አለመኖሩን ተገንዝበው የውስጥ አሰራራቸውን ጠብቀው በሐገር ጉዳይ ግን የጋራ አቋም በመያዝ ለውይይቱ እራሳቸውን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል

## ወጣቱን ትውልድ የሐገርና የወገን ፍቅር እንዲኖረውና ማድረግና በትግሉ ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርግ ማድረግ።

እወነት እንነጋገር ከተባለ ባሁኑ ወቅት አብዛኛው ወጣት ስለ ሐገር ጉዳይ እንዴት ነው ተብሎ ሲጠየቅ፣ እባካችሁ ተዉኝ ፖለቲካ ማውራት አልወድም ወይም አለፈልግም የሚል መልስ ነው የሚሰማው። ይህ ማለት ደግሞ ሁሉም ወጣት ነው ማለት አይደለም፡ ባሁኑ ወቅት ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ወጣቶች የሉም ማለት አይደለም፡ አሉ። ግን ብዙሃኑ የፍርሀት ይሁን ወይንም ተስፋ የመቁረጥ ራሳቸውን ሲያገሉ ነው የሚታዩት። እርግጥ ነው እኛ ትላልቆቹ በመጀመሪያ ካለፈው ስህተታችን በመማር ልባችንን ከፈት አምሮአችንን ሰፋ አድርገን በመስማማትና በመደማመጥ ደካማ ጎናችንን በማጠናከር ወጣቱን ወገናችን ከኛ ጥሩ ነገር እያየና እየተሳበ ሐገሩንና ወገኑን የሚወድ ትውልድ የማረግ ሃላፊነቱ የሁላችንም ነው። አለበለዚያ ግን እኛም በራሳችን እያዘንን ወጣቱ ትውልድም በእኛ እያዘነብን፣ ሐገራችንንም ምንም ለውጥ ሳይታይባት እንደውም ጭራሽ ድህነቷ እየባሰባት የልመናና የረሃብ ምሳሌ አድርገናት ለሚቀለው ትውልድ የምናስተላልፋት ከሆነ ትውልድም ይፍረድብናል።

እንግዲህ ከላይ የዘረዘርኳቸውን ችግሮቻችንና በመጠኑም ቢሆን መፍትሔ ሃሳቦች ይሆናሉ ያልኳቸውን በመነሻነት ሁላችንም በመገንዘብ አብረን በመስራት ወደፊት የምንጓዝበትን መንገዶች ማጠናከር እና ውጤቱንም ለማየት የምንበቃበትን ጊዜ ላማሳጠር ሁላችንም የተቻለንን እንሞክር። በተናጠል ወይንም ግለሰቦችንም ሆነ ቡድኖችን በማምለክ ያሳለፍነው ጊዜ ውጤቱ ምን እንደሆነ አይተነዋልና፣ ወደፊትም ሥልጣን ይዞ ለሕዝብ ተገዝቶ ሕዝብን በሚፈለገው መንገድ የሚመራ መንግስት ለማየትም ዋስትና አይኖረንም። ስለዚህ ሁላችንም በሐገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምንኖር በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ስር አንድ ሆነን ከተሰባሰብን ድምፃችን የጎላና በምንም ሆነ በምን ሕዝብን አስተዳድራለሁ ብሎ ሥልጣን የሚይዝ መንግሥት ፈላጭ ቆራጭ የማይሆንበትን፣ አስተማማኝ የሆነ ሕዝብ ድምጹን ሰጥቶ የራሱን መሪ የሚመርጥበትን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በሐገራችን

ለማስፈን አነድነታችን መሰባሰባችን መወያየታችን መተዋወቃችን ተዋውቀንም በመካከላችን መተማመን መፍጠር ከሁሉ በላይ አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ። ለዚህም ነው በኦባንግ ሜቶ ‘የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄ’ ጥላ ስር ሁላችንም በመሰባሰብ ከሁሉ ነገር ሰብአዊነታችንን እና ከዛም ኢትዮጵያዊነታችንን አስቀድመን ለአንዲት ሐገር አንድነት እድገትና ሕልውና እንረባረብ።

ይህንን ሙሉ በሙሉ የራሴ የሆነውን ሐሳብ በመደጋፍም ሆነ በመቃወም ወይንም ጠቃሚ ነው የምትሉትን በውስጡ ያላካተትኩትን ሐሳብ ለመሰንዘር የምትፈልጉ እንነጋገርበት እንወያይበት፣ የናንተንም ለመስማት ዝግጁ ነኝ። ከላይ ከጠቀስኳቸው ውስጥ ስህተቶች ካሉም ለመታረም ዝግጁ ነኝ። ምናልባት የማከብረው መንድሜን የአቶ ኦባንግ ሜቶን ሐሳብ አዛብቼ አቅርቤ ከሆነ የኔ የራሴ በትክክል አለመገንዘቤ (mis-understanding) ሆኖ እንዲታይልኝ በማክበር አሳስባለሁ። በዚሁም አጋጣሚ ወንድሜ ኦባንግን በመላው ዓለም በመዞር የታፈነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ድምፅ ለዓለም ሕዝብ እንዲያስተጋባ ያለእረፍት ለሚያደርገው ትግል አድናቆቴን ልቸር እወዳለሁ። ልክ እነደሱም በምትችሉት ሁሉ አስፈላጊውን ትግል ለምታደርጉት ሁሉ ቀጥሉበት በርቱ እንበርታ እላለሁ።

ከዚህም በላይ የበለጠ ለመረዳትና ግንዛቤ ለማግኘት www.solidaritymovement.org የሚለው ድህረ ገፅ ውስጥ ገብቶ ማንበብ ይቻላል።

እንወያይበት እንነጋገርበት።

ተባብረን የኢትዮጵያን ትንሣዔ እናፋጥን

ከምስጋና ጋር ፡ ቸር ይግጠመን፡ ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ።

ስለሺ ዘእንግልጣር